



# በልሳን መጸለይ




# ሰይጣን ክርስቲያኖችን የጸሎትን ቋንቋ (ልሳንን) ከመቀበል እንዴት እንደሚከለክል።


**satan has had a very successful campaign in preventing Christians from getting the Gift of Tongues. There are so many lies and misunderstanding in the church about this gift.**






ሰይጣን ክርስቲያኖችን የልሳንን ጸጋ እንዳይቀበሉ ስኬታማ ዘመቻ ይዟል።


ስለዚህ ጸጋ ብዙ ውሸቶችና አለመረዳቶች በቤተክርስቲያን ውስጥ አሉ።




በአጭሩ፥ ሰይጣን ቤተክርስቲያን እንዲነጋገሩበት፥ እንዲወያዩበት፥ እንዲያጠኑት፥ ጥሩ የሆነ ትምህርታዊ ውይይት እንዲያደርጉበት ይፈቅዳል፥ ነገር ግን ፈጽመው እስካልተቀበሉት ድረስ።




አንድ ወታደር ስለመሣሪያ አጠቃቀም ብዙ እውቀት ቢኖረው ነገር ግን ምንም (መሣሪያ) ከሌለው ምን ጥቅም አለው።





ይህን ጸጋ አለመጠቀሟ ቤተክርስቲያንን አሽመድምዷታል፥አብዛኞቹን አማኞች ከፍ ወዳለው የጸጋ ስጦታዎች እንዳያድጉ አግዷቸዋል። እግዚአብሔር የሰጠንን ጸጋ የምንጠቀምበት ጊዜ አሁን ነው።




ክርስቲያን ከሆኑና እስካሁን ጸጋው ከሌሎት…

አግኙት! (ተቀበሉት!)




ለምን እንደማትፈልጉት አልያም እንዴት ለማግኘት እንዳልተሳካላችሁ ምክንያት መደርደራችሁን አቁሙ÷

በቃ አግኙት!




እናም ስጦታው ያላችሁ ከሆነ…


ተጠቀሙበት።

አጎልብቱት

ዝም ብሎ ከተቀመጠ ምንም ጥቅም አይኖረውም።





እስቲ ክርስቲያኖችን ይህን ጸጋ እንዳይቀበሉ ያገዳቸውን አንዳንድ ውሸቶች እንመልከት።




ውሸት ቁ.1፡

ከሰይጣን ነው፥ ሰይጣን ነው በእናንተ አድሮ እየተናገረ ያለው።




በመጸሐፍ ቅዱስ ላይ በልሳን የመናገር ጸጋ ከሰይጣን ነው የሚል ምንም ዓይነት ምሳሌ የለም።

*ማንም በእግዚአብሔር መንፈስ ሲናገር “ኢየሱስ የተረገመ ነው” የሚል እንደሌለ፥ በመንፈስ ቅዱስም ካልሆነ በቀር “ኢየሱስ ጌታ ነው” ሊል አንድ ስንኳ እንዳይችል አሁን አስታውቃችኋለሁ።* 1ኛ ቆሮንቶስ 12፥3

*በልሳን ብጸልይ መንፈሴ ይጸልያል* 1ኛ ቆሮንቶስ 14፥14

ስለዚህ የልሳን ጸጋ ከሰይጣን አይደለም።

# Lie #2: It's not for Everyone




**ውሸት ቁ.2**

**ለሁሉም አይደለም።**




በዚህ አስተሳሰብ ላይ ያለው ስህተት፥ በመጀመሪያዋ ቤተክርስቲያን ሁሉም በልሳን የመጸለይን ጸጋ ተቀብለዋል።





**በሐዋርያት ሥራ ምዕ. 2 ላይ ያለውን እስኪ እንመልከት**

*በዓለ ኀምሳ የተባለውም ቀን በደረሰ ጊዜ፥ ሁሉም በአንድ ልብ ሆነው አብረው ነበሩ... በሁሉም መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው፥ መንፈስም ይናገሩ ዘንድ እንደሰጣቸው በሌላ ልሳኖች ይናገሩ ጀመር።*

[የሐዋርያት ሥራ 2፥1-2]





እናም አንድ መጋቢ (ፓስተር) ጓደኛዬ እንደነገረኝ፥ የማነቃቂያ (ሪቫይቫል) ጉባኤ እየመራ ሳለ 300 ሰዎች ወደ ፊት መጥተው ይህንን ጸጋ ተቀበሉ። እናም ሲጸልይ፥ 300ውም ሰዎች ጸጋውን ተቀበሉ። ታዲያ ይህ ጸጋ ለአንዳንዶች ብቻ የሚሆንበት ግን ለሁሉም የማይሆንበት አጋጣሚዎች ምንድን ናቸው። ለመቀበል እምነት ላለው ለሁሉም ይሰጠዋል።





ውሸት ቁ.3፡

አንዴ ሞክሬያለሁ፥ አልሠራም፥ ልቀበለው አልችልም።




በእኔ ልምድ፥ ቀለል ያለ የ5 ደቂቃ ጸሎት ይህን ጸጋ ለመቀበል በቂ ላይሆን ይችላል። ምንአልባት አንዳንድ የተቀቡ መጋቢዎች በዛ ፍጥነት ሊያደርጉት ይችላሉ፥ ነገር ግን ለእኔ፥ ያ ሰው ለመቀበል ብዙ መግፋትና አጠንክሮ መጸለይ እንዳለበት፡ አይቻለሁ። [በመንፈስ ቅዱስና በእሳት የሚያጠምቀው የናዝሬቱ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው። የጌታ አገልጋዮች ለሚቀበለው ሰው ሊጸልዩለት፡ ይችላሉ።]




ሰዎችን ይህን ጸጋ እንዲቀበሉ ማስተማር እንዲቀበሉት እምነታቸውን ያጠነክረዋል። ለመቀበል ከ1 ሠዓት በላይም መጸለይ ሊኖርባችሁ ይችላል።

ስለዚህ ታገሱ።

[ተርጓሚው፥ እኔ ይህን ጸጋ የተቀበልኩ እለት በቤቴ ውስጥ ሆኜ ስጸልይ ወደ 1ሠዓት አካባቢ ያህል ቆይታ ውስጥ ነበር። ስለዚህ በአንድ ጊዜ ካልተሳካ እንዳትታክቱ። መጾምና እምነትን ሙሉ በሙሉ በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ መጣል ደግሞ አስፈላጊ ነው።]





በተለምዶ ይህን ጸጋ ለመቀበል የሚያስቸግራቸው ሃይማኖታዊ ሰዎች ናቸው፥ ምክንያቱም አእምሮኣቸው እንዴት ሊቀበሉት እንደማይችሉ፥ አልያም ለምን እንደማያስፈልጋቸው፥ አልያም ለምን ጠቃሚ እንዳልሆነ፥ ብዙ ዓይነት መንፈሳዊ በሚመስሉ መከራከሪያዎች ስለተሞላ ነው።




**በልሳን የመጸለይን ጸጋ ከተቀበልኩ በኋላ፥ በሚቀጥለው ቀን ለመጀመር ተቸገርሁ። ስለዚህ እንዳጣሁት አጥብቄ አሰብሁ።**

***“ኦህ አይሆንም፥ የሆነ ኃጢአት ሠርቼ መሆን አለበት፥ አልያም የሆነ ስህተት እናም አሁን ጸጋውን አጣሁ።”***




ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ ሮሜ 11፥29 ላይ እንዲህ ይላል፥ የእግዚአብሔር ጸጋዎች የሚደንቁ ናቸው፥ ማለትም መልሶ አይወስዳቸውም። የሆነ ስህተት ሠርታችኋል ማለት ጸጋውን ታጡታላችሁ ማለት አይደለም። ይልቁንም፥ አንድ ክርስቲያን በኃጢአት ሊኖር ይችላል፥ እንደዛም ሆኖ ግን የሚያስደንቁ የጸጋ ስጦታዎችን ሊለማመድ ይችላል። [እለት እለት በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ኑሩ በቅድስና በጽድቅና በንጽህና። ክርስቲያን ሁሉ ጌታ ኢየሱስን በፍጹም ልቡ በፍቅርና እንደ እግዚአብሔር ቃል መኖር አለበት።]




የልሳን ጸጋ መዳናችሁን አያረጋግጥም።

አንድ ክርስቲያን ጸጋው ላይኖረው ነገር ግን ገነት ሊገባ ይችላል፥እናም ሌላ ክርስቲያን ደግሞ፥ጸጋው ኖሮት ወደ ሲዖል ሊገባ ይችላል። ስለዚህ መንፈሳዊ ጸጋዎች በትምክህት የተሞላችሁ እንዲያደርጓችሁ አትፍቀዱ።

እናም አስታውሱ፥ጸጋውን ልታጡ አትችሉም፥ነገር ግን ለረዥም ጊዜ ካልተጠቀማችሁበት፥እንግዲያው በ(2ኛ ጢሞቴዎስ 1፥6) እንደተገለጸው የእግዚአብሔርን ጸጋ ልታነቃቁ ይገባል።




እንደጓደኛዬ ምስክርነት፥በቺካጎ ጎዳናዎች ላይ እየሰበከ ሳለ አንድ ሴተኛ አዳሪ አጋጠመችው፥ ምናልባትም በእጽ ደንዝዛ ነበር። ይህች ሴት ኢየሱስን ተቀበለችና በቅጽበት በልሳን መናገር ጀመረች።




እናም ወዲያውኑ፥እጇን ወደ ላይ ዘርግታ በተሰጣት የጸሎት ቋንቋ ተጠቅማ እግዚአብሔርን እያመሰገነች በመንገዱ ወደ ላይና ወደ ታች ትመላለስ ጀመር።

እርሷ ልትቀበለው ከቻለች፥እናንተም ትችላላችሁ!




ውሸት ቁ.3፡

አያስፈልገንም።

እናም እውነታው፥ ይህ የከፋው የሰዎች ጥበብ ነው። እግዚአብሔር ለቤተክርስቲያን የማያስፈልጋትን ጸጋ ሊሰጣት ግራ አልተጋባም። በእውነት በቤተክርስቲያን የማያስፈልገን ነገር የሰዎች ጥበብ ነው።




አብዛኞቹ አብያተ ክርስቲያናት ከተፈጥሮአዊ በላይ በሆነው (ሰማያዊ ኃይል) እየሠሩ አይደለም።

ምንም ራዕይ የለም÷

ምንም ትንቢት የለም÷

ምንም ተአምር የለም÷

ምንም ፈውስ የለም÷

ምንም ነጻ መውጣት የለም÷

ምንም መታደስ (መነቃቃት) የለም




1ኛ ቆሮንጦስ 4፥20 **የእግዚአብሔር መንግሥት የወሬ ጉዳይ አይደለም፥ ነገር ግን የኃይል ነው።**

**የእግዚአብሔር ኃይል በአቢያተ ክርስቲያናት እንዲሠራ ያስፈልገናል።**





ውሸት ቁ.4፥

ጸጋው ከቀደመችው ቤተክርስቲያን በኋላ አብቅቷል (አቁሟል)።

አይደለም አላቆመም።

ሚሊየኖች ክርስቲያኖች ጸጋው አላቸው።




ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲህ አለ:- *የመኑትን እነዚህ ምልክቶች ይከተሏቸዋል፤ በስሜ አጋንንትን ያወጣሉ፤ በአዲስ ቋንቋ ይናገራሉ፤* (ማርቆስ 16 ፥17)

ስለዚህ፥ የልሳን ጸጋ አላለቀም (አላቆመም።)




ውሸት ቁ.5፡

ለየት ያለ (ያልተለመደ) ነው!

እውነታው ግን፥ እንዴት ክርስቲያን ልትሆኑና ከተፈጥሯዊው የላቀውን ነገር ልትፈሩ ትችላላችሁ። ይህ ማለት ልክ ዓሣ አጥማጅ ሆኖ ውኃን እንደመፍራት ያህል ነው። ክርስቲያን ከተፈጥሯዊው የላቀውን መቋቋም መቻል አለበት።




ይህ ሰዎችን መፍራት ብቻ ነው።

ሰውን መፍራት፥ ክርስቲያኖችን ከተፈጥሯዊው በሚልቀው፡እንዳይሠሩ፡ያግዳቸዋል።





የእህቴ የጸሎት ቋንቋ ወጣ ያለ ይመስላል፥ ከተለመደው ቋንቋ ጋር ፈጽሞ አይመሳሰልም። እናም ብዙ ሰዎች ፌክ እንደሆነ ሳይገምቱ አልቀሩም፤፤ ነገር ግን አንድ ቀን በኢኒዩት (Inuit) ቋንቋ፥ ያልተለመደ የኢስኪሞ ኢንዲያን ቋንቋ፥ የሚናገር ሰው አጠገብ ተቀመጠች። የእህቴን የጸሎት ቋንቋ ከሰማ በኋላ እንዲህ አላት፥ “*አንቺ ሴት፥ ለመሆኑ የምትናገሪውን ነገር ታውቂዋለሽ?... **ለእግዚአብሔር** እጅግ ደስ የሚል ጸሎት እያቀረብሽ ነው።*” ስለዚህ፥ ምንም እንኳ የጸሎት ቋንቋዋ ያልተለመደ ቢመስልም፥ ነገር ግን ትክክለኛ ነበር። ስለዚህ የጸሎትን ቋንቋ በሰው ጥበብ አትመልከቱ (አትፍረዱ፥) ምክንያቱም እንደተለመደው ዓይነት አይደለም።

አንዳንዴ ክርስቲያኖች የጸሎት ቋንቋ ኖሮኣቸው ላያውቁት ይችላሉ።




እናም ተጠንቀቁ፥ሰይጣን አካባቢያቹ ያሉትን ሰዎች ተጠቅሞ ጸጋችሁን ከመጠቀም ሊያሳንፋችሁ ይችላል።




ውሸት ቁ.6፡

የእኛ ቤተክርስቲያን መንፈሳዊ ስጦታዎች ላይ አታተኩርም።

ይህ "እኛ መንፈሳዊ ስጦታዎችን ቸል እያልን ነው" እንደማለት ያለ ሀይማኖታዊ አገላለጽ ነው።





አንድ ቤተክርስቲያን “እኛ ይቅርታ ላይ አናተኩርም” ወይም “እኛ ቅድስና ላይ አናተኩርም” ስትል አስቡት (ሳሉት።)




እስቲ አንዳንድ የጸሎት ቋንቋን ጥቅሞች እንመልከት።

መንፈሳችሁን ያንጻል ይገነባል።




*በልሳን የሚናገር ራሱን ያንጻል፤…*([1ኛ ቆሮንቶስ 14 ፥4](#))

*እናንተ ግን ወንድሞች ሆይ፥ከሁሉ ይልቅ በተቀደሰ ኃይማኖታችሁ ራሳችሁን ለማነጽ እየተጋችሁ በመንፈስ ቅዱስም እየጸለያችሁ፥*([ይሁዳ 1 ፥20](#)) (የእንግሊዘኛው መጽሐፍ ቅዱስ (KJV) በመንፈስ ቅዱስ እየጸለያችሁ ራሳችሁን ገንቡ ይለዋል።)




**እስቲ ጳውሎስን እንመልከት፥ እምነቱ በጣም ጠንካራ ነበረ፥እንዲህ አለ ......**

***ከእናንተ ይልቅ በልሳኖች ስለምናገር እግዚአብሔርን አመሰግነዋለሁ።*** [1 ቆሮንቶስ 14፥18]

**ለጳውሎስ መልካም ከሆነ ለእናንተ ደግሞ መልካም ነው።**




እንደ ብዙ ምስክርነቶች፥ የልሳን ጸጋ ክፉ መናፍስትን ያግዳል። እናም ይህ ስጦታ ብዙ ጊዜ ነጻ ለማውጣት፥ ክፉ መናፍስትን ለማስወጣት ይጠቅማል። መልካሙን ውጊያ ከሰይጣን ጋር ለመዋጋት ከፈለጋችሁ፥ በመንፈስ ቅዱስ መጸለይ ታላቁ፡ መሣሪያ፡ ነው።





የጸሎት ቋንቋ ጌታ የመጀመሪያዋን ቤተክርስቲያን የጀመረበት ነው።

በሐዋርያት ሥራ 2 ሁሉም ሐዋርያት በአንድ ቦታ በአንድነት ነበሩ፥ በመንፈስ ቅዱስ ተሞሉ በልሳንም ተናገሩ።

እናም በዛ 1 (፩) ቀን፥3000 የሚያህሉ ሰዎች ወደ ኢየሱስ መጡ።





መልካም፥ እንግዲህ እግዚአብሔር የመጀመሪያዋን ቤተክርስቲያን የጀመረበት መንገድ ያ ከሆነ፥ ስለዚህ ለእኛም ይህን የመጀመሪያውን ደረጃ መዝለል አስተዋይነት፡አይደለም።





ይልቁንም፥ ጌታ እንዲህ አለ፥

…*ከሰማይ ኃይልን እስክትቀበሉ ድረስ ጠብቁ።*


ሉቃስ 24፥49




እውነታው ይህ ነው ብዙ ክርስቲያኖች ተዳክመዋል፥ ምክንያቱም ከሰማይ ኃይልን ስላልተቀበሉ! በራሳቸው ጥንካሬ ነው እየሠሩ ያሉት፥ በእግዚአብሔር አይደለም። ስለዚህም ምንም እንኳን ኢየሱስ ሸክሜ ቀላል ቀንበሬ ልዝብ ነው (ማቴዎስ 11፥30) ቢልም፥ እግዚአብሔርን ሲያገለግሉ ድካምና ከአቅማቸው በላይ የተጫነባቸው ያህል ይሰማቸዋል። እነዚህ ክርስቲያኖች ከሰማይ ኃይልን ሊታጠቁ ይገባቸዋል! ያ ነው የእግዚአብሔር አላማ።




በአብዛኞቹ ሁኔታዎች፥(በሁሉም አይደለም) ታላላቅ መንፈሳዊ ስጦታዎች ያሏቸው ክርስቲያኖች መጀመሪያ የጀመሩት በጸሎት ቋንቋ ነው። ምክንያቱም ስለሚያንጽና እምነታቸውን ስለሚገነባ።





የጸሎት ቋንቋ ሰውየውን ለብዙ ሠዓታት እንዲጸልይ ያግዘዋል።

ከጸሎት ቋንቋው ጻጋ በፊት፥ የእኔ የጸሎት ጊዜ 15 ደቂቃ አካባቢ ብቻ ነበር። ከ15 ደቂቃ በኋላ፥ አእምሮዬ ሊያስበው የሚችለውን ሁሉ ብዬ ጨርሳለሁ፥የምጸልየው ነገር ያልቅብኛል።


ነገር ግን በዚህ ጻጋ ለብዙ ሠዓታት ለመጸለይ ችያለሁ፥አንዴ በልሳን አንዴ በተፈጥሮ ቋንቋዬ እያቀያየርኩ።





ብዙ የሙሉ ሌሊት ጸሎቶች ላይ ተካፍያለሁ፥ ብዙውን ጊዜ በእነዚህ የሙሉ ሌሊት ጸሎቶች ላይ መጸለይ የሚችሉት ይህ የልሳን ጸጋ ያላቸው ክርስቲያኖች፡እንደሆኑ፡ተረድቻለሁ።




እናም የዚህ የጸሎት ቋንቋ መኖር ሌላው ጥቅም፥ አንድ ጊዜ ካገኛቹት፥ ሌሎችም እንዲያገኙት መጸለይ ትችላላችሁ። ልክ ኢየሱስ በዮሐንስ 3፥6 እንደተናገረው፥ መንፈስ መንፈስን ይወልዳል። እንደውም ክርስቲያኖች፥ ለሌሎች ለማካፈል የሚያካፍሏቸውን መፈለግ አለባቸው፥ ኢየሱስ እንዳለው፥ በነጻ ተቀብላችኋል፥ በነጻ ስጡ።




# የጸሎትን ቋንቋ እንዴት ማግኘት ይቻላል?




*…መንፈሳዊ ስጦታዎችንም በብርቱ ፈልጉ*

1 ቆሮንቶስ 14 ፥1





**ጸጋውን እየተጠቀመ ያለ ቤተክርስቲያን ወይም ቡድን መፈለግ**

**የእኔ ቤተክርስቲያን ይህንን ጸጋ እያከፋፈለች አልነበረም፥ ስለዚህ ጸጋውን ለመቀበል ወደ ሌላ ቤተክርስቲያን መሄድ ነበረብኝ።**


**(አስተውሉ፤ ይህ ጸጋ ከእግዚአብሔር ነው፥ ስለዚህም ትቀበሉት ዘንድ ሙሉ በሙሉ እምነታችሁን በእርሱ ላይ አድርጉ እንጂ ሰዎችን አትመልከቱ።)**




ጸጋውን እንድትቀበሉ እንዲጸልዩላችሁ ጠይቋቸው።




ነገር ግን እንዳትታክቱ፥ እኔ እንዳየሁት ሰዎች ጸጋውን እንዲቀበሉ ማድረግ ልክ ልጅን እንደመውለድ ያህል ነው። ለብዙ ሰዎች በ5 ደቂቃ ብቻ አይሆንላቸውም። እኔ አንድ ሰው ጸጋውን ከመቀበሉ በፊት ብዙ ጊዜ ከሌሎች ጋር ለ1 ሠዓት ያህል አጽንቼ መጸለይ አለብኝ።




“*ልሳንን ማስቆም*” ከተባለ አጋንንት ተጠንቀቁ፥ ይህ በብዙ ክርስቲያኖች መካከል ያለ የኃይማኖት መንፈስ ነው። አንድ ሰው የልሳንን ጸጋ ሊቀበል ሲል፥ ይህ ክፉ መንፈስ የጸሎትን ቋንቋ እንዳይቀበሉ ኃይማኖታዊ በሚመስሉ መከራከሪያዎች አእምሯቸውን ያጥለቀልቀዋል፥ የልሳንን ጸጋ እንዳይቀበሉ ከማስፈራራትና ከመረበሽ ጋር። አብዛኞቹ የኃይማኖት መሪዎች በእናንተ ቤተክርስቲያን ይህ የኃይማኖት መንፈስ ቢኖራቸው አይግረማችሁ።

እኔ ራሴ ነበረብኝ።




አንድ መጋቢ የልሳንን ጸጋ እንድቀበል እየጸለየልኝ ሳለ፥ ወዲያው መጠቀም እንደጀመርኩኝ፥ ኃይለኛ ድምጽ ወደ አእምሮዬ መጣ፥ የኃይማኖት መንፈስ “*አቁመው፥ ኦ ይሄ እኮ የውሸት ነው፥ የማይመስል ነገር ነው፥ ይህ ከእግዚአብሔር አይደለም፥ ራስህ ነህ እያደረግኸው ያለኸው። ዝም ብለህ እየተንተባተብህ ነው፥ እንደዚህ አይደለም የሚጸለየው!*” ይለኝ ነበር።

ይህን ድምጽ ዝም ለማሰኘት መታገል ነበረብኝ፥ እናም ፍርሀቶቼን ሁሉ ቸል ማለት። ይህንን ስጦታ እንድትቀበሉ የሰይጣንን ድምጽ ቸል ማለት አለባችሁ።




ታዲያ ምን እየጠበቃችሁ ነው?




ሰበብ መደርደር አቁሙና አሁኑኑ

# ተቀበሉት!

www.DivineRevelations.info/TONGUES

**በመንፈስ ቅዱስ አብሮን ለሠራ ለአምላካችን ለእስራኤል ቅዱስ የናዝሬቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ክብር ምስጋና ይሁን፥ አሜን።**

ከእንግሊዘኛ ወደ አማርኛ ትርጉም ሙሉነህ አዲሱ
Translated to Amharic by Muluneh Addisu Abdissa,
matoughen@gmail.com